በአሜሪካን አገር የአጭር ጊዜ ቆይታ ለማድረግ ለሚያመለክቱት ቪዛ መሟላት ያለባቸው ነገሮች፡፡

በድረገፅ (በኢንተርኔት መስመር Online) የሚሞላው አዲሱ የጉበኝት ቪዛ ማመልከቻ ቅጽ አሞላልና የቃለ መጠይቅ ቀጠሮ መያዣ ሂደት የሚከተሉትን ሦስት ቅደም ተከተሎች ያካተተ ነው፡፡

1 ማመልከቻ ፤ በድረገፅ (በኢንተርኔት መስመር Online) ላይ ያለውን የማመልከቻ ቅጽ መሙላትና ማተም፣
2 የቀጠሮ ቀን፤ በድረገፅ (በኢንተርኔት መስመር Online) ላይ ያለውን የቀጠሮ ቅጽ መሙላትና ማተም፣
3 ክፍያ ፤ የቪዛ ማመልከቻውን ክፍያ ከታች በተጠቀሱት ከሦስት በአንዱ የአቢሲኒያ ባንክ ቅርንጫፎች መፈጸም ናቸው፡፡

የማመልከቻውን ቅጽ በድረገፁ (በኢንተርኔት መስመር Online) ላይ በሚከተለው መረጃ መሠረት ይሙሉ፤

- **http://addisababa.usembassy.gov** የሚለውን የኤምባሲውን ድረገፅ ይክፈቱ፡፡ ቀጥለውም **"Visa to the U.S.", "How to apply", "Electronic Visa Application Form (EVAF)"** የሚሉትን ገፆች በመክፈት የማመልከቻውን ቅጽ ይሙሉ፡፡
- በዚህ ገፅ መጨረሻ ላይ **"DS-156 Nonimmigrant Visa Application"** የሚለውን ሲጫኑ አዲስ የማመልከቻ ቅጽ ይመጣልዎታል፡፡
- በቅጹ ላይ የሚገኙትን እያንዳንዱን ጥያቄ መመለስ ይኖርቦታል፡፡ ስምዎን ሲሞሉ የአያት ስም፤ የእርስዎ መጠሪያ ከነአባት ስም ልክ ፓስፖርቱ ላይ እንደተፃፈው መሞላት አለበት፡፡ በተቻለ መጠን በቅፁ ላይ የሚገኙት ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ መሞላት ይኖርባቸዋል፡፡ በጥያቄ ተራቁጥር 15 ላይ አድራሻውን ሲሞሉ ወረዳ ወይም ክፍለከተማ፤ ቀበሌና የቤት ቁጥርዎን ይሙሉ ለዚህ ጥያቄ መልስ የፖ.ሳ.ቁ ቁጥር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በጥያቄ ተራቁጥር 16 ላይ ቢያንስ አንድ የስልክ ቁጥር መጥቀስ ይኖርብዎታል፡፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መረጃዎች ካልተሞሉ ማመልከቻዎ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
- ሁሉንም ጥያቄዎች ሞልተው ሲጨርሱ፣ በቅጹ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን **"Continue"** የሚለውን ሳጥን ይጫኑ፡፡ በዚህ ጊዜ የሞሉትን ጥያቄዎች ሁሉ የሚያሳይ 3 ገፅ የተሞላ ቅጽ ይታዮታል፡፡
- የሞሉትን ፎርም ሦስቱንም ገፆች ካተሙ በኋላ ሦስተኛው ገጽ ላይ በመስመሮች የተደገፈ ቁጥር **(Barcode)** መያዙን ያረጋግጡ፡፡
- ዕድሜያቸው ከ16-45 የሆኑ ወንድ አመልካቾች "DS-157" የተሰኘ ተጨማሪ ቅጽ መሙላት አለባቸው፡፡ ይህንን ቅጽ ለማግኘት ወደ ኤምባሲው ድረገፅ የመጀመሪያ ገፅ ተመልሰው **"Visa to the U.S."**, ከዚያም **"How to apply"**, የሚለውን በመክፈት **"Supplemental Form DS-157"** የሚለውን ቅጽ ከሞሉ በኋላ **DS-156** ከሚለው ቅጽ ጋር አያይዘው ያቅርቡ፡፡
- የሚያመለክቱተ ለትምህርት ወይም ለተወሰነ ጊዜ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ **(Student/Exchange Visitor Visa)** ከሆነ **DS-158** የተሰኘ ተጨማሪ ቅጽ መሙላት ይኖርብዎታል፡፡ ይህንን ቅጽ ለማግኘት ወደ መጀመሪያው የኤምባሲው ድረገፅ በመመለስ "Visa to the U.S.", ከዚያም "How to apply", የሚለውን ይጫኑ፡፡ ቀጥሎም "Contact Information and Work History" የሚለውን ቅጽ በሚገባ ይሙሉ፡፡ በመጨረሻም ይህንን ቅጽ አትመው DS-156 ከሚለው ቅጽ ጋር አያይዘው ያቅርቡ፡፡

ቀጠሮ ለመያዝ በድረገፁ (በኢንተርኔት መስመር Online) ላይ በሚከተለው መረጃ መሠረት ይሙሉ፤

- ቀጠሮ ለማስያዝ መጀመሪያ http://addisababa.usembassy.gov/how_to_apply_for_niv.html የሚለውን ይክፈቱ::
- በ online-service ሥር የሚገኘውን Make an appointment የሚለውን ይጫኑ:: Schedule Appointment የሚለውን ሳጥን ከኮዱ በታች ያለውን ይጫኑ::
- በኢንተርኔት መስመር Online የሚሞላውን ቅጽ (EVAF) በገፅ ሦስት ላይ የሚገኘውን የBar Code ቁጥር ከሞሉ በኃላ Submit የሚለውን ይጫኑ:: (ከዚህ በላይ ስለማመልከቻው ቅጽ በሚያስረዳው ርእስ ሥር 5ኛውን ነጥብ ይመልከቱ):
- ለቀጠሮ ክፍት የሆነውን ቀን ይጫኑ:: ለዚህ ዓይነት ቪዛ የማመልከቻ የቀጠሮ ቀናቶች ሰኞ ወይንም እሮብ ናቸው:: በመቀጠል መረጃ የሚጠይቅ ሌላ ገጽ ይመጣል::
- ያለውን የቀጠሮውን ቀን ይምረጡ:: ሙሉ ስም ከነአያት፣ የፓስፖርት ቁጥር፣ እና ሙሉ አድራሻዎን ማለትም ስልክ ቁጥር እና የኢሜል አድራሻ /ካለዎት/ ይሙሉ::
- Submit የሚለውን ይጫኑ:: NIV Appointment system –Appointment Confirmation የሚል ገጽ ሲታይዎት ገጹን ያትሙ:: አቢሲኒያ ባንክ ሄደው ክፍያውን ሲፈጽሙ ይህንን የቀጠሮ ማረጋገጫ ቅጽ ማሳየት ይኖርቦታል:: በቀጠሮዎ ቀን ወደ ኤምባሲ ሲመጡ ይህንኑ ቅጽ ይዘው መምጣት አይዘንጉ::

በአቢሲኒያ ባንክ የማመልከቻ ቅጽ ለማስገባትና ክፍያ ለመፈጸም የሚከተለው መረጃ ይከተሉ፤

1. የማመልከቻው ክፍያ ለመፈጸም ወደአቢሲኒያ ባንክ ቅርንጫፎች (ዑራኤል፣አራዳ ወይንም ራጉኤል) ቀጥሎ የተዘረዘሩትን በመያዝ ይሂዱ::
   - ባለ ሦስት ገፅ በEVAF (ኢንተርኔት መስመር Online) የተሞላውን የማመልከቻ ቅጽና አንድ ፎቶግራፍ፤ (ስለ ፎቶግራፍ ዓይነት መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ድህረገፅ ይመልከቱ http://addisababa.usembassy.gov/photo_requirements.html)
   - እድሜአቸው 16 - 45 ለሆኑ ወንዶች DS-157 ቅፅ መሞላት አለበት:: ለትምህርት ለተወሰነ ጊዜ የልምድ ልውውጥ ለማረግ (Student/Exchange Visitors) ለሚጓዙ አመልካቾች DS-158 ቅጽ መሞላት ይኖርበታል::
   - የሚያመለክቱት ለትምህርት ወይም ለተወሰነ ጊዜ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ (Student/Exchange Visitors Visa) ከሆነ I-20 ወይም DS 2019 ከ SEVIS ጋር ይዘው መቅረብ ይኖርቦታል::
   - ፓስፖርትዎ ቢያንስ ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት የሚያገለግል መሆን አለበት::
   - ያተሙት የቀጠሮ ማረጋገጫ ቅፅ መያዝ ይኖርቦታል::
   - የማይመለስ $131 የአሜሪካን ዶላር ወይንም በጊዜው ባለው የምንዛሪ መጠን እኩል የሆነውን የኢትዮጵያ ብር መክፈል ይጠበቅብዎታል::
2. ቀጠሮዎ ሰኞ ከሆነ ከሰኞ በፊት እስካለው ሀሙስ ከሰዓት 10:30 ድረስ እሮብም ከሆነ ከሱ በፊት እስካለው ሰኞ ከሰዓት 10:30 ድረስ በተጠቀሱት አቢሲኒያ ባንክ ቅርጫፎች ሄደው መክፈል ይኖርብዎታል::
3. የማመልከቻ ሰነድ በትክክል ያልተሟላ ሆኖ ባንኩ ማመልከቻዎን ሳይቀበል ሲቀር በሌላ ጊዜ መረጃዎቹን አሟልተው መመለስ ይኖርቦታል::
4. የቀጠሮ ወረቀትዎን፣ ፓስፖርትዎን፣ ፎቶግራፍን ለባንኩ ያስረክባሉ:: ባንኩ ተገቢ የሆኑ ማናቸውንም እርማቶች ካካሄደ በኃላ ፓስፖርትዎንና የቀጠሮ ወረቀትዎን ይመልስልዎታል::
5. ለባንኩ $131 ዶላር ወይንም በጊዜው ባለው የምንዛሪ መጠን እኩል የሆነውን የኢትዮጵያ ብር ሲከፍሉ ባንኩ ባለሁለት ገፅ ደረሰኝ (አንዱ ነጭ እና ሁለተኛው ቢጫ ኮፒ) ይሰጥዎታል:: ይህም ደረሰኝ ለአንድ ዓመት የሚያገለግልና በዚሁ ዓመት ለሁለተኛ ወገን መተላለፍ የሚችል ነው::
6. ለቃለ መጠይቅ በቀጠሮው ቀንና ሠአት ወደ ኤምባሲው ሲመጡ ፓስፖርትዎን፣የቀጠሮዎን ወረቀትና ገንዘብ የከፈሉበትን ሁለት ገፅ ደረሰኝ ይዘው መቅረብ ይጠበቅብዎታል::